የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፷፫
አዲስ አበባ ሐምሌ ፯ ቀን ፪ሺ.፲፪ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

26th Year No.63
ADDIS ABABA 14th July, 2020

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ.፪፻፲፫/፪ሺ.፲፪ ዓ.ም

የማዕድን ሥራዎች አዋጅ(ማሻሻያ) አዋጅ ............ ..........................................ገጽ ፲፪ሺ.፮፻፸፮

## Content

Proclamation No.1213/2020

Mining Operations (Amendment) Proclamation ...........................................Page 12,676

### አዋጅ ቁጥር ፩ሺ.፪፻፲፫/፪ሺ.፲፪

### <u>የማዕድን ሥራዎች አዋጅን ለማሻሻል</u> <u>የወጣ አዋጅ</u>

የማዕድን ሥራዎች አዋጅን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፡

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

፩. **<u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "የማዕድን ሥራዎች አዋጅ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፩ሺ.፪፻፲፫/፪ሺ.፲፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. **<u>ማሻሻያ</u>**

የማዕድን ሥራዎች አዋጅ ቁጥር ፮፻፸፰/፪ሺ.፪ (በአዋጅ ቁጥር ፰፻፲፮/፪ሺ.፮ እንደተሻሻለው) እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

፩/ የአዋጁ አንቀጽ ፲፩ ንዑስ አንቀጽ (፫) ሥር የሚከተሉት አዲስ ፊደል ተራ (መ) እና (ሠ) ተጨምረዋል፡-

### PROCLAMATION No.1213 /2020

### <u>A PROCLAMATION TO AMEND THE MINING OPERATIONS PROCLAMATION</u>

WHEREAS, it has become necessary to amend the Mining Operations Proclamation;

NOW, THERFORE, in accordance with Article 55 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1 **<u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the "Mining Operations (Amendment) Proclamation No. 1213/2020."

2. **<u>Amendment</u>**

The Mining Operations Proclamation No. 678/2010 as amended by Proclamation No.816/2013 is hereby amended as follows:

1. The following new paragraphs (d) and (e) are added under Sub-Article (3) of Article 11 of the Proclamation:

"መ) ለኢንደስትሪ ግብዓትነት የሚውሉ ወይም ከማጌጫ ድንጋዮች ውጭ ያሉ እንደ አሸዋ፣ ጠጠር፣ ገረጋንቲ እና የመሳሰሉት የኮንስትራክሽን ማዕድናት ሲሆን ኢትዮጵያዊ ዜግነት የሌለው ሰው፡፡"

"d) a non-citizen of Ethiopia, construction minerals excluding those used as raw material and dimension stones such as sand, aggregate, selected materials and others."

"ሠ) ቢያንስ ፳፭ በመቶ የሚሆን የአክሲዮን ድርሻ ከያዘ የሃገር ውስጥ ባለሃብት ጋር በጋራ በመሆን የከፍተኛ ደረጃ የደለል ማዕድን ማምረት ሥራ ላይ ለመሰማራት ከሚፈልግ የውጭ ባለሃብት በስተቀር በሌላ በማንኛውም የደለል ማዕድን ሥራ ላይ ለመሰማራት የሚፈልግ የውጭ ባለሃብት፡፡"

"e) except a foreign investor who would like to engage in large scale placer mining in partnership with a domestic investor holding a minimum of 25% share, a foreign investor who would like to engage in any other placer mining operation."

፪. የአዋጁ አንቀጽ ፶፩ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፶፩ ተተክቷል፡-

2. Article 51 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Article 51:

"፩/ በማዕድን ዘርፍ የማማከር አገልግሎት ሥራ ላይ መሠማራት የሚፈልግ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወይም ትውልደ ኢትዮጵያዊ ተገቢውን የማመልከቻ ክፍያ በመክፈልና የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት ለሚኒስቴሩ ማመልከት ይችላል፡፡

"1/ Any Ethiopian or Ethiopian Origin who wishes to engage in providing consultancy service in the mining sector may apply to the Ministry for a certificate of competence by paying the appropriate application fee and completing the appropriate form.

፪/ በማዕድን ዘርፍ እንደድሪሊንግ፣ የላቦራቶሪ ወይም ማዕድናትን ከማዕድን አዘል አፈር ወይም አለት መለየት ባሉት የቴክኒክ አገልግሎት ሥራ ላይ መሠማራት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ተገቢውን የማመልከቻ ክፍያ በመክፈልና የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት ለሚኒስቴሩ ማመልከት ይችላል፡፡

2/ Any person who wishes to engage in providing technical service such as drilling, laboratory or residue stockpile separating service in the mining sector may apply to the Ministry for a certificate of competence by paying the appropriate application fee and completing the appropriate form.

፫/ በማዕድን ዘርፍ የመሥክ ሥራ ላይ እንደ ሕክምና፣ ድንኳን መትከል ወይም ምግብ ማዘጋጀት በመሳሰሉ የቴክኒክ አገልግሎት ሥራ ላይ መሠማራት የሚፈልግ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወይም ትውልደ ኢትዮጵያዊ ተገቢውን የማመልከቻ ክፍያ በመክፈልና የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት ለሚኒስቴሩ ማመልከት ይችላል፡፡

3/ Any person who wishes to engage in providing technical service in fieldwork such as health, camping and catering service in the mining sector may apply to the Ministry for a certificate of competence by paying the appropriate application fee and completing the appropriate form.

፬/ ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)፣ (፪) እና (፫) የተመለከቱት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ የብቃት ማረጋገጫ የምሥክር ወረቀት ማመልከቻውን ተቀብሎ ይመዘግበዋል።"

4/ The Ministry shall accept and register the application for certificate of competence if the requirements specified in Sub-Article (1), (2) and (3) of this Article are met."

፫. የአዋጁ አንቀጽ ፹፪ ሥር የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፬) ተጨምሯል፡-

3. The following new Sub-Article (4) is added under Article 82 of the Proclamation:

"፬. ይህ አዋጅ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ለኢንደስትሪ ግብዓትነት የሚውሉ ወይም ከማጋጌጫ ድንጋዮች ውጭ ያሉ እንደ አሸዋ፣ ጠጠር፣ ገረጋንቲ እና የመሳሰሉት የኮንስትራክሽን ማዕድናት እንዲሁም የደለል ማዕድን ሥራን በሚመለከት ለውጭ ባለሀብት የተሰጠ ፈቃድ ወይም ከውጭ ባለሀብት ጋር የተደረገ የማዕድን ማምረት ስምምነት ፀንቶ ለሚቆይበት ቀሪ ዘመን የፀና ይሆናል። ሆኖም የፈቃዱ ወይም የስምምነቱ ዘመን አብቅቶ ሲታደስ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ይፈፀማል።"

"4. A mining license or mining agreement issued to a foreign investor or concluded with a foreign investor to mine construction minerals excluding those used as raw material and dimension stones such as sand, aggregate, selected materials and others, including placer mining operation prior to the coming into effect of this Proclamation shall continue in force for the remaining period of its validity. However, the renewal of the license or agreement upon expiry shall be made in accordance with the provisions of this Proclamation."

## ፫. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

## 3. <u>Effective Date</u>

This proclamation shall enter in to force on the date of publication in the *Federal Negarit Gazette.*

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፯ ቀን /፪ሺ፲፪ ዓ.ም**

**Done at Addis Ababa on this 14th Day of July, 2020**

**ሣህለወርቅ ዘውዴ**

**SAHLEWORK ZEWDE**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**